# የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ

# ምዝገባ አዋጅ

# ቁጥር ………/፪ሺ፫

<u>የመጨረሻ ረቂቅ</u>

www.chilot.me

## የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ምዝገባ አዋጅ ቁጥር ………../፪ሺ፫

የኮንስትራክሽን ዘርፍ ድህነትን በመቀነስ፣ መሰረተ ልማቶችን በመገንባት እና ሰፊ የሥራ ዕድሎችን በመፍጠር ለአገሪቱ ኢኮኖሚ ጠቃሚ ሚና የሚጫወት በመሆኑ፣

በመንግስታዊ ዘርፉ ከፍተኛ ወጪዎች የሚመደብለት እና የግል መዋዕለ ንዋይ የሚደረግበት የግንባታ ሥራዎች በብቃት እና ኤኮኖሚያዊ በሆነ የሐብት አጠቃቀም በጥራት እና በወቅቱ አከናወኖ ማስረከብ የሚችል ኃላፊነት በሚሰማው እና ብቃት ባላቸው ሙያተኞች እና ድርጅቶች መከናወን ያለበት በመሆኑ፣

የዘርፉን ጤናማ ዕድገቶች የሚጎዱ መልካም ያልሆኑ ገፅታዎችን ለመከላከል ሙያዊ ሥነ ምግባርን እና ዲሲፕሊን ማስፈን አስፈላጊ በመሆኑ ምክኒያት፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ ፶፭(፩) መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

### <u>ክፍል አንድ</u>
### <u>ጠቅላላ</u>

### ፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ምዝገባ አዋጅ ቁጥር ………../ ፪ሺ፫ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. <u>ትርጓሜ</u>

(ሀ) የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/ “አመልካች” ማለት ኮንስትራክሽን ወይም ተዛማጅ የኮንስትራክሽን ሥራ ላይ ለመሰማራት ፈልጎ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት ማመልከቻ ያቀረበ ሙያተኛ ወይም ድርጅት ነው፡፡

፪/ “የንግድ ፈቃድ” ማለት በንግድ ምዝገባ እና ፈቃድ አዋጅ አዋጅ ቁጥር ፷፻፹፮/፪ሺ፪ መሰረት የተሰጠ የንግድ ሥራ ፈቃድ ማለት ነው፡፡

፫/ “የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት” ማለት በዚህ አዋጅ እና በዚህ እና በንግድ ምዝገባ እና ፈቃድ አዋጅ መሰረት በሚወጡ ደንብ ወይም መመሪያ መሰረት የሚጠየቁ የትምህርት ደረጃን፣ የሰው ኃይል፣የቢሮ አገልግሎትን እና ቁሳቁሶችን ላሟላ የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ነው፡፡

፬/ “ሥራ ተቋራጭ” ማለት በኮንስትራክሽን ስራ ላይ የተሰማራ ሰው ወይም ድርጅት ነው፡፡

፭/ “ኮንስትራክሽን” ማለት ከመሬት በታች እና በላይ የሚከናወኑ ህንጻን እና የምህንድስና መሰረት ልማትን ጨምሮ በቋሚ ንብረቶች ላይ የዕቃዎች እና አገልግሎቶች ጥምር የሆነ የልማት፣ የማስፋፊት፣የመገጣጠም፣የጥገና፣የዕድሳት፣የማሻሻል፣የቁፋሮ፣የማወላለቅ እና የማፍረስ ተግባር ነው፡፡

፮/ “ተዛማጅ የኮንስትራክሽን ሥራ” ማለት ለኮንስትራክሽን ሥራ ተዛማጅ የሆኑ የአገልግሎት ወይም የአቅረቦት ሥራዎች ላይ በተሰማሩ ሰዎች የኮንስትራክሽን፣ ግብአቶች፣ መሳሪያዎችና መገልገያዎች አቅራቢ ፣ አስመጪ፣ ላኪ፣ ጅምላ፣ ንግድ፣ አከራይ የመሳሰሉትን ነው፡፡

፯/ “አማካሪ” ማለት የኮንስትራክሽን የቅድመ ግንባታ፣ዲዛይን፣ቁጥጥር እና ውል አስተዳደር አገልግሎቶችን የሚሰጥ ሰው ወይም ድርጅት ነው፡፡

፰/ “ሚኒስቴር” ወይም “ሚኒስትር” ማለት የከተማ ልማት እና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፡፡

፱/ “ድርጅት” ማለት በኮንስትራክሽን እና ተዛማጅ የኮንስትራክሽን ሥራዎች ላይ የተሰማራ የግል ንግድ ወይም የንግድ ማህበር የሆነ የንግድ ተቋም ነው፡፡

፲/ “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ወይም የህግ ሰውነት ያለው አካል ነው፡፡

፲፩/ “ፕሮጀክት” ማለት የኮንስትራክሽን ሥራዎች ውል ወይም ተከታታይ ወይም ተያያዥ የሆነ የኮንስትራክሽን ውል ማለት ነው፡፡

፲፪/ “ሙያተኛ” ማለት በምህንድስና፣በስነ ህንጻ እና ሌሎች የኮንስትራክሽን ሙያዎች የሰለጠነ ሰው ነው፡፡

፲፫/ “መዝገብ” ማለት የሙያተኛ፣የድርጅት፣የፕሮጀክት እና የተዛማጅ የኮንስትራክሽን ሥራዎች መዝገብ ነው፡፡

፲፬/ “የተመዘገበ ሙያተኛ” ማለት በዚህ አዋጅ በተገለፀው መሰረት ያሉትን ልዩ ልዩ መስፈርቶች አሟልቶ የተመዘገበ ሙያተኛ ነው፡፡

፲፭/ “ምዝገባ” ማለት በዚህ አዋጅ መሰረት ስም እና ሌሎች ዝርዝሮችን የያዘ የኮንስትራክሽን ሙያተኞች፣ተዛማጅ የኮንስትራክሽን ሥራ የሚሰሩና የሥራ ተቋራጮች ምዝገባ ነው፡፡

(ለ) ማናቸውም በወንድ ፆታ የተገለጹ አገላለፆች ሴት ፆታንም ይጨምራል፡፡

## ፫. ዓላማ

ይህ አዋጅ፡-

፩/ በኮንስትራክሽን እና ተዛማጅ የኮንስትራክሽን ሥራ ላይ ለተሰማሩ ግልፅነትን እና ተጠያቂነትን የሚያረጋግጥ የሙያተኛ፣ የድርጅት እና የስራዎች ምዝገባ እና ማረጋገጫ ሥርዓትን ማቋቋም፤

፪/ የኮንስትራክሽን ዘርፉ አገሪቱ የምትጠይቀውን የተሻሻለ ቅልጥፍና እና ብቃት፣ወጥነት ጥራት፣አፈጻጸም እና ጨርሶ ማስረከብ ለማሳደግ አስተዋፅኦ ማድረግ ፤

፫/ ለግል እና ለመንግስት ደንበኞች የኮንስትራክሽን ሥራዎች አፈፃፀም ያልተቋረጠ ማሻሻያዎች እና ክትትሎችን ግብ ያደረጉ ምርጥ የሆኑ ልምዶችን ተግባራዊ ያደረገ የሙያተኞች፣የሥራ ተቋራጮች፣ተዛማጅ የኮንስትራክሽን ሥራዎች እና የሌሎች ያገባኛል ባዮች ምዝገባ ሥርዓትን ማቋቋም፤

ዓላማዎች አሉት፡፡

፬. **<u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>**

ይህ አዋጅ በኮንስትራክሽን እና ተዛማጅ የኮንስትራክሽን ሥራ ዘርፍ ላይ በተሰማሩ

፩/ በሙያተኞች፣

፪/ በድርጅቶች

ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

፭. **<u>መዝጋቢ አካል</u>**

ይህን እና በዚህ አዋጅ መሰረት በሚወጡ ደንቦች የተገለጹት ሃላፊነቶችን እና ተግባራቶችን የሚያስፈፅም የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ መዝጋቢ አካል ማቋቋሚያ፣ ዝርዝር አደረጃጀት፣ ተግባር እና ኃላፊነት በደንብ ይወሰናል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>
## <u>የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት</u>

፮. **<u>የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ማግኘት ግዴታ ስለመሆኑ</u>**

፩/ ተቃራኒ ድንጋጌ ቢኖርም በዚህ አዋጅ መሰረት የሚሰጥ የብቃት የምስክር ወረቀት ካላገኘ በስተቀር ማንኛውም ሙያተኛ ወይም ድርጅት በኮንስትራክሽን ወይም ተዛማጅ የኮንስትራክሽን ሥራዎች ላይ መሰማራት አይችልም፡፡

፪/ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሳያገኝ ለማንኛውም በኮንስትራክሽን ወይም ተዛማጅ የኮንስትራክሽን ሥራ ላይ ለሚሰማራ ሙያተኛ ወይም ድርጅት የንግድ ፈቃድ መስጠት አይቻልም፡፡

፫/ በኮንስትራክሽን ወይም ተዛማጅ የኮንስትራክሽን ሥራ ለመስራት ከሙያተኛ ወይም ድርጅት ጋር ውል ማድረግ የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ሙያተኛው ወይም ድርጅቱ የጸና የብቃት ምስክር ወረቀት እና የንግድ ፈቃድ ያለው መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

፬/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) (፪) እና (፫) ቢኖርም ሚኒስቴሩ በዚህ ዓዋጅ መሰረት በሚወጣ መመሪያ በተወሰኑ ዓይነት ኮንስትራክሽኖች ላይ ተፈፃሚነት እንዳይኖረው ሊፈቅድ ይችላል፡፡

፯. **<u>የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ምድብ እና ደረጃ</u>**

የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለእያንዳንዱ ሙያተኛ እና ድርጅት የተለያየ ምድብ እና ደረጃ ይኖረዋል፡፡

፰. **<u>የምድብ እና የደረጃ ዓይነቶች</u>**

፩/ በሚከተሉት ዘርፎች የተለያዩ ምድቦች እና ደረጃዎች ያሏቸው ሥራ ተቋራጮች ይኖራሉ፣

(ሀ) ህንጻ

(ለ) መንገድ
(ሐ) የባቡር ሀዲድ
(መ) ኃይል
(ሠ) ውኃ እና
(ረ) በደንብ የሚገለፁ ሌላ ንዑስ-ዘርፎች የተለዩ ሥራ ተቋራጮች፡፡

፪/ በሚከተሉት ዘርፎች የተለያዩ ምድቦች እና ደረጃዎች ያሏቸው አማካሪዎች ይኖራሉ፣

(ሀ) ህንጻ
(ለ) መንገድ
(ሐ) የባቡር ሀዲድ
(መ) ኃይል
(ሠ) ውኃ እና
(ረ) በደንብ የሚገለፁ ሌላ ንዑስ-ዘርፎች የተለዩ ሥራ ተቋራጮች፡፡

፫/ በሚከተሉት ዘርፎች የተለያዩ ምድቦች እና እርከኖች ያሏቸው ሙያተኞች ይኖራሉ፣

(ሀ) ህንጻ
(ለ) መንገድ
(ሐ) የባቡር ሀዲድ
(መ) ኃይል
(ሠ) ውኃ እና
(ረ) በደንብ የሚገለፁ የሌላ ዘርፎች የተለዩ ሥራ ተቋራጮች ወይም ባለሙያዎች፡፡

፬/ በዚህ አዋጅ መሰረት በሚወጣ ደንብ የየምድቦቹ፣ ደረጃዎቹ እና እርከኖቹ መስፈርቶች ይወሰናል፡፡

፭/ ሙያተኛው ወይም ድርጅቱ ከላይ ከተገለፁት ዘርፎች አንድ ወይም ከዚያ በላይ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሊኖረው ይችላል፡፡

፮/ አንድን ፕሮጀክት ለማከናወን የሚያስፈልገውን ዝቅተኛ ገደብ በእያንዳንዱ ምድብ፣ደረጃ እና እርከን የመያዝ አቅምን ታሳቢ በማድረግ በደንብ ይወሰናል፡፡

፯/ ለጥቃቅን እና አነስተኛ ድርጅቶች ልዩ ምድብ እና ደረጃ በደንብ ይወሰናል፡፡

፰/ ለተዛማጅ የኮንስትራክሽን ሥራ ምድብ፣ደረጃ እና እርከን በደንብ ይወሰናል፡፡

፱/ በዚህ ዓዋጅ እና ይህንን አዋጅ መሰረት አድርጎ በሚወጣ ደንብ መሰረት ካልሆነ በስተቀር ለማንኛውም ሙያተኛ፣ድርጅት እና ተዛማጅ የኮንስትራክሽን ሥራ የምዘና መስፈርት ማውጣት አይቻልም፡፡

## ፱. <u>የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት ስለሚቀርብ ማመልከቻ</u>

፩/ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ ለዚሁ ተግባር በመዝጋቢው አካል በተዘጋጀ ቅፅ ተሞልቶ ይቀርባል፡፡

፪/ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት በእያንዳንዱ ሙያተኛ ወይም ድርጅት ሊቀርብ ይችላል፡፡

፫/ ለብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እያንዳንዱ አመልካች የሚከተሉትን ማስረጃዎች ማቅረብ አለበት፤

(ሀ) የትምህርት ማስረጃ፣
(ለ) ከዚህ በፊት በዘርፉ የነበረውን ልምድ የሚያሳይ ማስረጃ እንደ አስፈላጊነቱ፣
(ሐ) አግባብ ባለው አካል በሚከናውን ግምገማ የተሰጠ ውጤት፣
(መ) ሌሎች በዚህ አዋጅ መሰረት በሚወጣ ደንብ መሰረት የሚያስፈልጉ አግባብነት ያላቸው ሰነዶች፡፡

፬/ የብቃት ማረጋገጫ ፍቃድ ለማግኘት በድርጅት ሲቀርብ ለመመዝገብ ከሚፈልገው ምድብ እና ደረጃ ጋር የተያያዙትን የሚከተሉትን ማስረጃዎች ማቅረብ አለበት፣

(ሀ) በደንብ የሚወሰነው ዝቅተኛ የተመዘገቡ ሙያተኞች እና መሳሪያዎች ቁጥር እና ዓይነት፣
(ለ) በደንብ የሚወሰነውን ዝቅተኛ ዓመታዊ ክንውን ሂሳብ፣
(ሐ) ሌሎች በዚህ አዋጅ መሰረት በሚወጣ ደንብ የሚወሰን አግባብነት ያላቸው ሰነዶች፡፡

፭/ አንድን ፕሮጀክት ለማከናወን የሚያስፈልገውን ዝቅተኛ ገደብ በእያንዳንዱ ምድብ፣ደረጃ እና እርከን የመያዝ አቅምን ታሳቢ በማድረግ በደንብ ይወሰናል፡፡

## ፲. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለመስጠት

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፱ መሰረት የተደነገገውን አመልካቹ አሟልቶ ሲያቀርብለት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ ይሰጣል፡፡

፪/ የብቃት ምስክር ወረቀቱን መስጠት ያልተቻለ እንደሆነ አመልካቹ እንደ ሁኔታው የሚያስፈልጉትን እና መውሰድ ያለበትን አግባብነት ያላቸውን እርምጃዎች በፁሁፍ እንዲያውቀው ይደረጋል፡፡

## ፲፩. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ዕድሳት

፩/ ከላይ በአንቀፅ ፲ መሰረት የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለአንድ ዓመት ፀንቶ የሚቆይ ሲሆን የኢትዮጵያ ባጀት ዓመቱ ካለቀ በኃላ በሚቀጥሉት ሁለት ወራት ውስጥ መታደስ አለበት፡፡

፪/ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ የሚታደሰው ሙያተኛው ወይም ድርጅቱ በዚህ አዋጅ መሰረት የሥራ አፈጻፀሙ የሚያረካ መሆኑን ከተረጋገጠ በኃላ ነው፡፡

፫/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፪ መሰረት የተገለጹትን መስፈርቶች አርኪ ሆኖ ካልተገኘ የዕድሳት ጥያቄውን ውድቅ በማድረግ በ ፲ (አስር) ቀናቶች መውሰድ ያለበትን አግባብነት ያለቸውን እርምጃዎች በፁሁፍ ያስታውቀዋል፡፡

## ፲፪. የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለማገድ እና ስለመሰረዝ

የብቃት ማረጋገጫው ምስክር ወረቀት በማጭበርበር ወይም የተጭበረበሩ ሰነዶችን መሰረት ተደርጎ የተገኘ ከሆነ ወይም የምስክር ወረቀቱን የያዘው ሰው ይህንን አዋጅ የሚፃረር ተግባር በመፈፀሙ ተከሶ ከተፈረደበት ሊታገድ ወይም ሊሰረዝ ይችላል፡፡

# ክፍል ሦስት
# የሙያተኞች፣የድርጅቶች፣የፕሮጀክቶች፣የስራ አፈፃፀም እና የተዛማጅ የኮንስትራክሽን ሥራዎች ምዝገባ፡፡

## ፲፫. የሙያተኞች እና የድርጅቶች ምዝገባ

፩/ በዚህ አዋጅ መሰረት በሚወጣ ደንብ የሙያተኛ እና የድርጅት ስም፣ ምድብ፣ደረጃ፣አርከን ዓይነት የብቃት ማረጋገጫ የተሰጠበት ቀን፣መደበኛ የስራ ቦታ እና ሌሎች ዝርዝሮችን የያዘ መዝገብ ይቋቋማል፡፡

፪/ ማንኛውም ሙያተኛ

(ሀ) አእምሮው ጤነኛ

(ለ) ምግባረ ብልሹነትን በሚያመለክት ወንጀል ተከሶ የተቀጣ ካልሆነ በስተቀር ይመዘገባል፡፡

፫/ የሙያተኞችን የምዝገባ መዝገብ በድረ ገፅ ጭምር ለህዝብ ክፍት ይደርጋል፡፡

## ፲፬. የቅጥር ሙያተኞች ምዝገባ

፩/በኮንስትራክሽን ላይ የተሰማራ ማንኛውም ድርጅት የሚቀጥራቸውንም ሆነ የሚያሰናብታቸውን ሙያተኞች በፁሁፍ የማስታወቅ ግዴታ አለበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፩ ላይ የተመለከተው ግዴታ መከበሩን ለማረጋገጥ እንደአስፈላጊነቱ የቅድሚያ ማስታወቂያ መስጠት ሳያስፈልገው ድርጅትን መጎብኘት እና ማንኛውንም ሰነድ መመርመር ይችላል፡፡

፫/ የመዝጋቢው አካል ሰራተኞች ስለሚያካሂዱት ጉብኝት፣ ሰነዶች ምርመራ ወይም የማረጋገጥ ተግባር እና ሪፖርት አቀራረብ ስነ ስርዓቶች አስመልክቶ በደንብ ይወሰናል፡፡

፬/ ያለመዝጋቢው አካል የቅድሚያ ስምምነት ማንኛውም ድርጅት የሚከተሉትን ሰዎች በቅጥር ሙያተኝነት ቀጥሮ ማሰራት አይችልም፣

(ሀ) በመዝገብ ላይ ያልተመዘገበን ወይም ስሙ ከመዝገብ ላይ የተፋቀን ሰው፣

(ለ) በሙያው ምግባረ ብሉሽነት በወንጀል ተከስሶ የተፈረደበትን ሰው እና

(ሐ) የመንግስት ሰራተኛ የሆነ፡፡

## ፲፭. የፕሮጀክቶች ምዝገባ

፩/ በዚህ አዋጅ መሰረት በሚኒስቴሩ በሚወጣ መመሪያ ሁሉም የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች ስም፣ጠቅላላ ዋጋ፣ የስራ ደረጃ እና ሌሎች ዝርዝሮችን የያዘ መዝገብ ይቋቋማል፡፡

፪/ ማንኛውም ሙያተኛ፣ ድርጅት፣ እና አሰሪ አካል ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ላይ በሚወስነው ስነ ስርዓት መሰረት ስለ ፕሮጀክቶች ሪፖርት የማቅረብ እና የማስመዝገብ ግዴታ አለበት፡፡

፫/ የፕሮጀክቶችን የምዝገባ መዝገብ በድረ ገፅ ጭምር ለህዝብ ክፍት ያደርጋል፡፡

## ፲፮. <u>የስራ አፈፃፀም ምዝገባ</u>

፩/ ለሁሉም የኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶች የስራ አፈፃጸሙን፣

(ሀ) ቁልፍ የአፈፃፀም አመላካች የሆኑ እና ተባብሮ በመስራት፣በወቅቱ በማስረከብ፣የጤና እና የደህንነት ግንዛቤን ለገንዘብ የሚሰጥን ዋጋ፣የአገልግሎት ጥራትን፣ስልጠናን፣ ምርታማነትን እና ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ላይ የሚመለከቱ ሌሎች ዝርዝሮችን የሚያካትቱ የአሰሪውን እርካታ፣

(ለ) በማንኛውም ፕሮጀክት ላይ የተከሰቱ አደጋዎች ቁጥር እና ዓይነት፣ የደረሰው አደጋ እና ያስከተለው ጥፋት እና ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ላይ የሚመለከቱ ሌሎች ዝርዝሮችን በማካተት የሚገልፁ ይሆናሉ፡፡

፪/ ማንኛውም ሙያተኛ፣ ድርጅት፣ እና አሰሪ አካል ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ላይ በሚወስነው ስነ ስርዓት መሰረት ስለ ሥራዎች አፈፃፀም እና አደጋዎች ሪፖርት የማቅረብ እና የማስመዝገብ ግዴታ አለበት፡፡

## ፲፯. <u>የተዛማጅ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ምዝገባ</u>

፩/ በዚህ አዋጅ መሰረት በሚወጣ ደንብ የተዛማጅ ኮንስትራክሽን ሥራዎች፣ ምድብ፣ ደረጃ፣ እርከን፣ የብቃት ማረጋገጫ፣ የተሰጠበት ቀን፣መደበኛ የስራ ቦታ እና ሌሎች ዝርዝሮችን የያዘ መዝገብ ይቋቋማል፡፡

፪/ የተዛማጅ ኮንስትራክሽን ሥራዎች አገልግሎቶች ዓይነት፣ የመሳሪያዎች እና የማሽኖች መጠን፣መለያ፣ብቃት እና ዓይነት፣ይመዘግባል፣ያረጋግጣል ማስረጃ ይሰጣል፣ይቆጣጠራል፡፡

# <u>ክፍል አራት</u>
# <u>ስለቅሬታ</u>

## ፲፰. <u>የቅሬታ ኮሚቴ</u>

፩/ የሚከተሉት አባላት የሚኖሩት የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ምዝግባ ቅሬታ ኮሚቴ (ከዚህ በታች "ኮሚቴ" እየተባለ የሚጠራ) ይኖራል፣

(ሀ) ኮሚቴው በሚኒስትሩ የሚሰየሙ ሁለት ተወካዮች፣
(ለ) የኮንስትራክሽን ሙያተኛ እና ድርጅት ማህበራት ሁለት ተወካዮች፣
(ሐ) የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተወካይ

፪/ የአንድ አባል የስራ ዘመን ሁለት ዓመት ሲሆን የኮሚቴው ሰብሳቢ ከአባላቱ ውስጥ በሚኒስትሩ ይሰየማል፡፡

## ፲፱. <u>የኮሚቴው ሥልጣን እና ተግባራት</u>

ኮሚቴው፤

፩/ ይህን አዋጅ ወይም በዚህ አዋጅ መሰረት የሚወጣውን ደንብ፣ መመሪያ እና የኮንስትራክሽን ዘርፍ የስነ ምባር ደንብ በመተላለፍ በሙያተኛ ወይም በድርጅት ላይ የሚቀርብ ክስን ተቀብሎ ያጣራል፣ይመረምራል፣

፪/ በሙያተኛው እና ድርጅት ላይ የቀረበውን ክስ ለማየት የሚያበቃ ማስረጃ መኖሩን ሲያረጋግጥ ሙያተኛው ወይም ድርጅቱ በ፳ (ሃያ) ቀናት ውስጥ እንዲያቀርብ በመጥሪያው ላይ በመግለፅ ክሱን ለሙያተኛው ወይም ለድርጅቱ ይልካል፡፡

፫/ በሙያተኛው ወይም በድርጅቱ ላይ የቀረበውን ክስና ማስረጃ እንዲሁም በሙያተኛው ወይም በድርጅቱ በኩል የተሰጠውን መልስና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ፣

(ሀ) ክሱ ተገቢ ካልሆነ ወይም በበቂ ማስረጃ ካልተደገፈ ክሱን በመሰረዝ ሙያተኛው ወይም ድርጅቱ እንዲሰናበት፣
(ለ) ክሱ ተገቢና በማስረጃ ተደገፈ ከሆነ እንደጥፋቱ ክብደት ሙያተኛው ወይም ድርጅቱ፣

(፩) የፁሁፍ ማስጠንቀቂያ እንዲሰጠው፣
(፪) ከአምስት ዓመት ላልበለጠ ጊዜ ከሥራው እንዲታገድ፣
(፫) ለሙያተኛው ከ፶ ሺ (ሃምሳ ሺህ ብር) ያልበለጠ ለድርጅት ከ፩፻ሺ (አንድ መቶ ሺህ ብር ያልበለጠ ቅጣት እንዲጣልበት፣
(፬) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ተሰርዞ ከመዝገብ እንዲፋቅ
(፭) ተገቢ ነው ያላቸውን ሌሎች ውሳኔዎች እንዲሰጥ፣

፬/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፫) መሰረት ተገቢውን ውሳኔ እስኪወስድ ድረስ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን ሊያግድ ይችላል፡፡

፭/ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሙያተኛው ወይም ድርጅት ላይ የሚጣለውን ቅጣት ክብደት ለመወሰን የወንጀል ሪኮርድ፣ የሙያተኛውን ወይም የድርጅቱን የግል ማህደር ወይም ሌላ ተመሣሣይ ማስረጃ መስማትና መመርመር ይችላል፡፡

፮/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፫) (ለ) መሰረት የተሰጠው ማንኛውም ውሳኔ በሙያተኛው ወይም በድርጅቱ የግል ማህደር ውስጥ እንዲመዘገብ ይደረጋል፡፡

፯/ የሙያተኛ እና የድርጅት የስነ ምግባር ብቃት የሚጎለብትበትን የኮንስትራክሽን ሙያ ክብር የሚጠበቅበትን ሁኔታ እያጠና ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፡፡

፰/ የቀረበውን ማንኛውም ክስ ክሱ በቀረበ ከስድስት ወራት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የመጨረሻ የውሳኔ ሃሳብ ለሚኒስትሩ ያቀርባል፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ ጉዳዩን ለማጠናቀቅ የማይቻልበት በቂ ምክኒያት ሲያጋጥም ምክኒያቱን በፁሁፍ በመግለፅ ከሦስት ወራት የማይበልጥ ተጨማሪ ጊዜ እንዲፈቀድለት ሚኒስትሩን በፁሁፍ መጠየቅ ይችላል፡፡

## ፳. <u>የኮሚቴው ስብሰባ</u>

፩/ ኮሚቴው እንደ አስፈላጊነቱ በማናቸውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል፡፡

፪/ የኮሚቴው አባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ ከተገኙ ምልአተ ጉባኤ ይሆናል፡፡

፫/ የኮሚቴው ውሳኔዎች በአብዛኛው የድምፅ ብልጫ ያልፋሉ ሆኖም ድምፅ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል፡፡

፬/ በዚህ አንቀፅ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚቴው የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ፳፩. የሚኒስትሩ ሥልጣን

፩/ ሚኒስትሩ በቅደም ተከተል በአንቀፅ ፩፱ (፳) ላይ ከኮሚቴው የቀረበውን ሃሳብ ከመረመረ በኃላ ተገቢውን ውሳኔ ይሰጣል፡፡

፪/ ኮሚቴው በአግባቡ ያላጣራው ወይም ያላጤነው ፍሬ ነገር ወይም ማስረጃ ካለ ይህው ተጣርቶ ወይም ተገናዝቦ እንዲቀርብለት ለኮሚቴው ለአንድ ጊዜ መመለስ ይችላል፡፡

## ፳፪. በሚኒስትሩ ውሳኔ ላይ ስለሚቀርብ ይግባኝ

፩/ ሚኒስትሩ የሠጠው ውሳኔ ስህተት ያለበት ሆኖ ከተገኘ በውሳኔው ቅር የተሰኘው ወገን ውሳኔው በደረሰው በ፳ ቀናት ውስጥ ይግባኙን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡

፪/ ፍርድ ቤቱ ወደ ፍሬ ነገር ሳያገባ በሕግ ጉዳይ ላይ ውሳኔ በመስጠት ጉዳዩን ወደ ሚኒስትሩ ይመልሰዋል፡፡

፫/ የሚኒስትሩ ውሳኔ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ ከተገኘ ሚኒስትሩ የፍርድ ቤቱን ውሳኔ መሰረት በማድረግ ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ ያደርጋል፡፡

# ክፍል አምስት
# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## ፳፫. የሙያተኛ እና የድርጅት ግዴታዎች

ማንኛውም ሙያተኛ እና ድርጅት

፩/ ይህንን አዋጅ በዚህ አዋጅ መሰረት የሚወጣውን ደንብና መመሪያ እና የሚሰጡትን ትዕዛዞችና ውሰኔዎች የማክበር፣

፪/ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ የሥነ ምግባር ደንቦችን ማክበር፣

፫/ ሙያውን እና የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውን ከሚያዋራድ ማናቸውም ተግባራት የመታቀብ፣

፬/ በኮንስትራክሽን ላይ ተፈጻሚ የሆኑ የጤና፣የጥንቃቄ እና የደረጃ ግዴታዎችን የመፈፀም፣

፭/ ኮንስትራክሽን በተፈለገው ጥራት እና በወቅቱ ተከናውኖ ርክክብ እንዲፈጸም ግዴታዎችን ማክበር እና ተገቢውን ትብብር ማድረግ፣

፮/ተገቢ የሆነ የአገልግሎት ክፍያ እና የትርፍ ህዳግ ማስከፈል፣

**፳፬. ቅጣቶች**

በዚህ አዋጅ መሰረት ሚኒስቴሩ የሚወስዳቸው አስተዳደራዊ እርምጃዎች እንደተጠበቁ ሆነው ጥፋቱ አግባብ ባለው ሌላ ሕግ የበለጠ የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር ወንጀሉ መፈፀሙ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ፡፡

፩/ የፀና የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሳይኖረው የኮንስትራክሽን አገልግሎት የሰጠ ወይም ለመስጠት የሞከረ ከብር ፩፻፶ሺ (አንድ መቶ ሃምሳ ሺ.ህ) እስከ ፫፻ሺ (ሶስት መቶ ሺ.ህ) በሚደረስ የገንዘብ መቀጮና እስከ ፯ (ሰባት) አመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

፪/ ማንኛውም ሰው ባልታደሰ፣በታገደ ወይም በተሰረዘ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አገልግሎት የሰጠ፣ ሰራተኛ የቀጠረ፣ ያልተመዘገበ ሙያተኛን ያሰራ ከብር ፩፻፶ሺ (አንድ መቶ ሃምሳ ሺ.ህ) እስከ ፫፻ሺ (ሶስት መቶ ሺ.ህ) በሚደረስ የገንዘብ መቀጮና እስከ ሰባት አመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡ ድርጅት ከሆነ በ፭፻ሺ (አምስት መቶ ሺ.ህ) ብር ይቀጣል፡፡

፫/ ማንኛውም ሰው ሆነ ብሎ የብቃት ማረጋገጫ ከሌለው ሰው ጋር የኮንስትራክሽን ውል ያደረገ ከሆነ በብር ፩፻፶ሺ (አንድ መቶ ሃምሳ ሺ.ህ) ብር የገንዘብ መቀጮ እና እስከ ፪ (ሁለት) ዓመት እስራት ይቀጣል፡፡

፬/ ማንኛውም ሰው ሆነ ብሎ ሓሰተኛ መረጃዎችን በማቅረብ በሙያተኛ እና በድርጅት የምዝገባ መዝገብ ላይ የተመዘገበ ወይም የብቃት ምስክር ወረቀት ካገኘ ወይም ካሳደሰ እስከ ፩፻፷ሺ ብር የገንዘብ መቀጮ እና እስከ ፲ (አስር) ዓመት ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

፭/ ማንኛውም ሰው ሆነ ብሎ ስለተቀጠሩ እና ስለተሰናበቱ የተመዘገቡ ሙያተኞች፣ፕሮጀክቶች እና የስራ አፈጻፀሞች ትክክለኛ መረጃ ወይም ዘገባ ሳያቀርብ ከቀረ ወይም በዚህ ዓዋጅ መሰረት የሚወጣ ደንብ ፣በሚኒስተሩ መመሪያ ላይ የሚጠይቁትን ካልፈፀመ እስከ ፷ሺ (ስድሳ ሺ.ህ ብር) የገንዘብ መቀጮ እና አስከ ፭ (አምስት) ዓመት ፅኑ አስራት ድረስ ይቀጣል፡፡

፮/ ከሙያተኛ እና ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ እና ከሙያተኛ፣ ከፕሮጀክቶች እና ከሥራ አፈፃፀም ምዝገባ ጋር በተያያዘ የሚሰራ ማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ እና ሹም ፣ጉቦ ከወሰደ ወይም በዝምድና ወይም በጥቅማ ጥቅም ወይም በሌላ ህገወጥ ግንኙነት የብቃት ማረጋገጫ የሰጠ፣ያደሰ፣ያሳደገ፣ያሻሻለ፣ምዝገባ ያከናወነ፣ በድርጅት ተቀጥሮ ሲሰራ የተገኘ የመንግስት ሰራተኛ ወይም ሹም አስከ ፷ሺ (ስድሳ ሺ.ህ ብር) በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ እና አስከ ፭ (ሰባት) ዓመት ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡

**፳፭. መረጃ የመስጠት ግዴታ**

ሁሉም ሙያተኛ እና ድርጅት ይህንን አዋጅ፣በዚህ አዋጅ መሰረት የሚወጡ ደንብ እና መመሪያ ለማስፈጸም አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

**፳፮. ቁጥጥር**

ሚኒስትሩ ይህንን አዋጅ ተግባራዊ መሆኑን ለማረጋገጥ በሙያተኛ እና በድርጅት ላይ ተገቢውን ቁጥጥር ለማድረግ መብት አለው፡፡ የቁጥጥሩን ስርዓት በተመለከተ ዝርዝሩ በደንብ ይወጣል፡፡

**፳፯. የመተባበር ግዴታ**

ይህንን አዋጅ ተግባራዊ ለማድረግ ማንኛውም ሰው የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

www.chilot.me

**፳፰. ደንብ የማውጣት ሥልጣን**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፳፱. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

ሚኒስቴሩ ይህንን አዋጅ እና በአንቀፅ ፳፰ መሰረት የሚወጡ ደንቦችን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፴. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ**

ሁሉም ሙያተኛ እና ድርጅት በዚህ አዋጅ ላይ እና በዚህ አዋጅ መሰረት በሚወጡ ደንቦችን እና መመሪያዎች ላይ የተመለከቱትን መስፈርቶች አሟልቶ አዋጁ ከፀናበት እለት ጀምሮ ባሉት ስድስት ወራቶች መመዝገብ፣የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ማውጣት እና ሌሎች ምዝገባዎችን መፈፀም አለበት፡፡

**፴፩. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡